# የካሣ ነገር

ታደለ ኣብርሃም

26/12/2009 ዓ.ም

ማንኛውም ማሕበረሰብ በኣባላቱ እንቅስቃሴ እና መስተጋብር ሂደት ወቅት በግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ለሚደርስ የኣካልም ሆነ የንብረት ጉዳት የሚያካክስበት የካሣ ስርዓት ኣለው፤ ከግጭት/ቅራኔ ኣፈታት መንገዶችም እንደ ኣንዱ ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል ።

የካሣ ኣወሳሰን ስርዓት በዘመናዊ የሕግ ማዕቀፍም የተካተተ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፤ ኣንድ ሰው ለምሳሌ በመኪና ተገጭቶ ጉዳት ከደረሰበት፣ ጉዳት ኣድራሹ የተጎጂውን የሕክምናና ሌሎች ወጪዎች ከመሸፈን በተጨማሪ በተጎጂው ላይ ለደረሰው የስነልቦና ስብራትና ስቃይም በገንዘብ ተተምኖ የመክፈል ግዴታ ይጣልበታል። በዚህ ጽሑፍ ለማየት የተፈለገው፣ በማሕበረሰብ ደረጃና በጦር ምክንያት ስለሚደርስ ጉዳትና ስለሚወሰነው ካሣ ሲሆን፣ ከታሪክ ዓለምኣቀፍ ኣብነቶችን ካየን በኋላ በሃገር ውስጥስ እንዴት ሊተገበር ይቻላል/ይገባል የሚለውን ሃሳብ ለማንሳት ይሞክራል ።

## ዓለም-ኣቀፍ ኣብነቶች

### *የ 1ኛው የዓለም ጦርነት የካሣ ክፍያዎች*

ሩስያኖች በብሬስት- ሊቶቭስክ ውል *መሠረት*(ከ 8 ወራት በኋላ ውሉ በቦልሼቪኩ *መንግስት* የተካደ ቢሆንም) ለማዕከላዊ *ኃይላቱ* ካሣ ለመክፈል ተስማምተው ነበር። ቡልጋርያ 2.25 ቢልየን የወርቅ ፍራንክ(90 ሚልየን *ፓ*ውንድ) በኖዪ ውል *መሠረት* ለሦስቱ *ኃ*ይላት ካሣ ከፍላለች ።

ጀርመንም በቨርሳይ ውል *መሠረት* 132 ቢልየን ወርቅ ማርክ ለሦስቱ *ኃ*ይላት እንደ ካሣ ለመክፈል ተስማምታለች። ነገር ግን ጀርመን የተጣለባትን ካሣ የተወሰነውን ከከፈለች በኋላ በ1932 መክፈሏን ኣቋርጣለች። ነገር ግን ይኼ ሁኔታ ጀርመንን ከባለዕዳነት ነፃ ሊያደርጋት ኣልቻለምና *የጀርመን የውጭ ዕዳዎች ስምምነት* በሚል እ.ኤ.ኣ. በ1953 ዓ.ም በተከለሰው ውል የካሣውን ገንዘብ እንድትከፍል ሆናለች። ዕዳውን መክፈሏ ሁለቱ ጀርመኖች እስኪዋሃዱ ድረስ ተቋርጦ ከቆየ በኋላ የዚህ ዕዳ የመጨረሻው ክፍያ እ.ኤ.ኣ. በኦክቶበር 3 ቀን 2010 ዓ.ም ተጠናቋል ።

### *የ 2ኛው የዓለም ጦርነት የካሣ ክፍያዎች በጀርመን*

በ 2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ናዚ ጀርመን ከያዘቻቸው ኣገራት፣ ክፍያዎችንና ንብረቶችን በተለያየ መንገድ ወስዳለች፤ ብድሮችም በግዴታ ወስዳለች፤ በተጨማሪም፣ ሃገራት የተፈጥሮ ሃብቶቻቸውንና የግዴታ የጉልበት ሥራ እንዲሰጡ ተገደዋል ።

ከ 2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ፣ እ.ኤ.አ. በጁላይ 17 እና ኦገስት 2 ቀን 1945 ዓ.ም መካከል በተካሄደው የፖትስዳም ኮንፈረንስ መሠረት፣ ጀርመን ለተባበሩት ኃይሎች 23 ቢልየን የአሜሪካ ዶላር ያክል ባብዛኛው በማሽኖችና የማምረቻ ፋብሪካዎች መልክ መክፈል ነበረባት። ለሶቭየት ሕብረት የሚከፈለው ካሣ እ.ኤ.አ. በ1953 ዓ.ም ቆሟል። ብዛት ያላቸው ፋብሪካዎች ተነቃቅለዋል ወይም ወድመዋል። በምዕራቡ ዓለም ፋብሪካና ማሽኖችን መነቃቀል የቆመው እ.ኤ.አ. በ1950 ዓ.ም ነው ።

ከጀርመን እጅ መስጠት በፊት ጀምሮ እና ለቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት፣ አሜሪካ "ዘመቻ የወረቀት አግራፍ" በመባል የሚታወቅ ጠንካራ የሆነ የቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ ዕውቀት እንዲሁም የፓቴንት ፍቃዶች እና በጀርመን የነበሩ ብዙ ግንባር-ቀደም ሳይንቲስቶችን የማሰባሰብ ፕሮግራም አካሂዳለች። የታሪክ ባለሞያው ጆን ጊምበል፣ *ሳይንስ ቴክኖሎጂ እና ካሣ - ብዝበዛና ዘረፋ በድሕረ-ጦርነት ጀርመን* በሚለው መፅሐፉ፣ በአሜሪካና ብሪታንያ የተወሰደው "ምሁራዊ ካሣ" በገንዘብ ሲተመን ወደ 10 ቢልየን የአሜሪካ ዶላር ይጠጋል ይላል። የጀርመን የካሣ ክፍያ በከፊል *በግዳጅ ሥራ* መልክ ነበር። በ 1947 በአማካይ 4,000,000 የጀርመን የጦር ምርኮኞች እና ሲቪል ሰራተኞች ("የካሣ ሰራተኞች" ወይም "የማጠናከሪያ ሰራተኞች" በሚሉ የተለያዩ ስያሜዎች) በሶቭየት ሕብረት፣ ፈረንሳይ፣ ብሪታንያ፣ ቤልጅየም እና በጀርመን በሚገኝና አሜሪካ በምታስተዳድረው "ወታደራዊ የሥራ አገልግሎት አሃዶች" ውስጥ እንደ ግዳጅ ሰራተኞች ሆነው አገልግለዋል ።

### *የ 2ኛው የዓለም ጦርነት የካሣ ክፍያዎች በጣልያን*

በ 1947ቱ የፓሪስ የሰላም ውሎች መሠረት፣ ጣልያን ለዩጎዝላቭያ 125 ሚልየን የአሜሪካ ዶላር፣ ለግሪክ 105 ሚልየን ዶላር፣ ለሶቭየት ሕብረት 100 ሚልየን ዶላር፣ ለኢትዮጵያ 25 ሚልየን ዶላር፣ እና ለአልባንያ 5 ሚልየን ዶላር ለመክፈል ተስማምታለች። ለኢትዮጵያ የተሰጠው ካሣ የቆቃ ኃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ እንደተሰራበት ይነገራል ።

### *ሌሎች የ2ኛው የዓለም ጦርነት ካሣዎች*

ፊንላንድ፣ 300 ሚልየን ዶላር ካሣ ለሶቭየት ሕብረት ለመክፈል ተስማምታለች። ሃንጋሪ 200 ሚልየን ዶላር ለሶቭየት ሕብረት፣ 100 ሚልየን ዶላር ለቼኮዝላቫክያ እና ዩጎዝላቭያ ለመክፈል ተስማምታለች። ሩማንያ 300 ሚልየን ዶላር ለሶቭየት ሕብረት ለመክፈል ተስማምታለች፤ ነገር ግን ሩማንያ በተለያየ መንገድ የከፈለችው ሂሳብ ቢሰላ ወደ 1.2 ቢልየን ዶላር ይጠጋል። ቡልጋርያ 50 ሚልየን ለግሪክ እና 25 ሚልየን ለዩጎዝላቭያ ለመክፈል ተስማምታለች ።

### *ጃፓን (የ 1895ቱ ቻይና-ጃፓን ጦርነት)*

የሺሞኖሰኪ ውል በኤፕሪል 17፣ 1895 የተፈረመ ሲሆን፣ ቻይና 200 ሚልየን የብር ሳንቲም (3.61 ቢልየን የን) ለጃፓን እንድትከፍል ግዴታ ተጥሎባታል፤ እንዲሁም የሻሺ፣ ቾንግቺንግ፣ ሱዡ፣ እና ሃንግዡ ወደቦች ለጃፓን የንግድ እንቅስቃሴ ክፍት እንድታደርግ ተስማምታለች ።

### *የ 2ኛው የዓለም ጦርነት የካሣ ክፍያዎች በጃፓን*

ከጃፓን በተደረገው የሰላም ውል (1951) አንቀጽ 14 መሠረት፣ "ጃፓን በጦርነቱ ጊዜ በእርሷ ምክንያት ለደረሰባቸው ጉዳትና ስቃይ፣ ለተባበሩት ኃይላት ካሣ መክፈል አለባት፤ ጃፓን ከተባበሩት ኃይላት ጋር ወዲያውኑ ወደ ድርድርና ስምምነት ትገባለች፤" ከጃፓን ጋር በተገባው በሳንፍራንሲስኮ የሰላም ውል (1951) መሠረት የተደረጉ የጦርነት ካሣዎች የሚከተሉትን ያካትታል፦ የካሣ መጠኑ 550 ሚልየን ዶላር (198 ቢልየን የን 1956) የሆነ ለፊሊፒንስ፣ 39 ሚልየን ዶላር (14.04 ቢልየን የን 1959) ለቬትናም ተከፍሏል፤ የጦር ምርኮኞችን ለመካስ 4.5 ሚልየን ፓውንድ ስተርሊንግ (4.54109 ቢልየን የን) ለዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ ተከፍሏል፤ እና ጃፓን 23.681 ቢልየን ዶላር (379.499 ቢልየን የን) የሚገመት በውጭ አገራት የሚገኙ ንብረቶቿን አስረክባለች።

ጃፓን የሰላም ውልን ከ49 ሃገሮች ጋር በ1952 ተፈራርማለች፤ 54 የሁለትዮሽ ስምምነቶችም አከናውናለች።.....

### *አሜሪካ*

በሬገን አስተዳደር ጊዜ የነበረው የአሜሪካ መንግሥት በ2ኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ላደረሰው ጉዳት በ1988 በኦፊሴል ይቅርታ ጠይቋል፤ ለተጎጂዎችና ለተወላጆቻቸውም ካሣ ከፍሏል ።

### *ኢራቅ እና ኩዌት*

ከባሕረ-ሰላጤው ጦርነት በኋላ፣ ኢራቅ በኩዌት ወረራ ወቅት ለደረሰው ጉዳት የኢራቅን የፋይናንስ ባለዕዳነት የሚያውጀውን የተባበሩት መንግሥታት የደህንነት ምክር ቤት ውሳኔ 687 ተቀብላለች። የተባበሩት መንግሥታት የካሣ ኮሚሽን (የተ.መ.ካ.ኮ.) ሲቋቋም፣ በተለያዩ መንግሥታት፣ ኮርፖሬሽኖችና ግለ-ሰቦች 350 ቢልየን ዶላር ያክል የካሣ ጥያቄ ቀርቧል። ለነዚህ ክፍያዎች የሚያስፈልገው ገንዘብ 30% ከኢራቅ የነዳጅ ዘይት ሽያጭ የሚገኝ ነበር። ነገር ግን የ 350 ቢልየን ዶላሩ የካሣ ጥያቄ በአንድ ጊዜ ሊሟላ የሚችል ስላልነበረ፣ በአያሌ ዓመታት ውስጥ ለማከናወን ዕቅድና ቅደም-ተከተል ማዘጋጀት አስፈልጓል። ለመንግሥታትና ድርጅቶች ወይም ኮርፖሬሽኖች (ሕጋዊ ሰዎች) ይልቅ ለተፈጥሮ ሰዎች ቅድሚያ መስጠቱ፣ "የዓለም-አቀፍ የካሣ ጥያቄ አተገባበር ሂደት ላይ ግልጽ የሆነ እድገት አምጥቷል" ሲል የተ.መ.ካ.ኮ. ገልጿል ።

በዚህ የካሣ ፕሮግራም የሚደረጉ ክፍያዎች ይቀጥላሉ፤ የተ.መ.ካ.ኮ. እንደሚገልጸው፣ እስከ ጁላይ 2010 ድረስ 18.4 ቢልየን ዶላር ለካሣ ጠያቂዎች ክፍያ ተፈጽሟል ።

## የሃገራችን ሁኔታስ ?

በሃገራችን የሃገር ምስረታ ሂደት ውስጥ ነፍጥ ያነገቡ ቡድኖች የተለያዩ ውጊያዎች እያካሄዱ መጥተዋል። ነፍጥ ባነገቡ ወታደሮች መካከል በሚካሄድ ፍልሚያ የሚደርስ ጉዳት ቅቡል ተደርጎ ይወሰዳል፤ ያም ሆኖ ግን በውጊያ ወቅት የምርኮኛ አያያዝን በተመለከተ፣ የሲቪል ማሕበረ-ሰብንና ተቋማትን ዒላማ ያለማድረግን በተመለከተ፣ ወዘተ. ሕጎች አሉ፤ በርግጥ ሕጎቹን የሚጥሱ ወገኖች አሉ፤ ለምሳሌ በ 1928ቱ የጣልያን ወረራ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ ዘምቶ

የነበረው የጣልያን ጀኔራል፣ የመርዝ ጭስ መጠቀም በዓለም ሕግ መሠረት ክልክል ነው ያስቀጣናል ብሎ ለሙሶሊኒ ሃሳብ ቢያቀርብ፣ ሙሶሊኒ "ጦርነት ሕግ የለውም፤ በፈለግከው መንገድ ተጠቅመህ ማሸነፍ ብቻ ነው ሕጉ፤ ስለዚህ የመርዝ ጭሱን ተጠቅመህ በቶሎ ጦርነቱን እንድታጠናቅቅና ድሉን እንድታበስረን" ብሎ እንዳዘዘው በዚህ ጉዳይ ላይ የተጻፉ የታሪክ ሰነዶች ያስረዳሉ። ያም ሆነ ይህ ግን ጦርነቱ ካለቀ በኋላ ሙሶሊኒ ከሚገባው ቅጣት ኣላመለጠም፤ ለኢትዮጵያም የጦር ጉዳት ካሣ ተፈጽሟል ።

በሃገራችን የረጅም ዘመን ታሪክ ነፍጥ ያነገቡ ቡድኖች እርስ በርስ ቢታኮሱና ቢገዳደሉም ነፍጥ ያላነገበ ሲቪል ማሕበረ-ሰብን ማጥቃትና ጉዳት ማድረስ ግን እንደ ነውር እና የጀግንነት ተቃራኒ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። ይኼ ባሕል ግን በሃገራችን በሦስት ተከታታይ መንግሥታት ተጥሶ እናገኘዋለን ።

### ***ኣፄ ምኒልክ***

ኣፄ ምኒልክ በ1881 ዓ.ም የኢትዮጵያ ን.ነ. ሆነው ከነገሱ በኋላ ኤርትራ የጣልያን ግዛት እንደሆነች በውጫሌ ውል መሠረት በሙሉ ስምምነት ኣፅድቀውለታል። በራሳቸው ኣስተዳደር ሥር የቀረውን የትግራይን ክልል ሕዝብ ግን ለዘራፊዎችና የጦር ኣበጋዞች ሸኩቻ ተጋልጦ እያለ ችላ ብለው ትተውታል፤ የወቅቱ ዕውቅ ፀሓፊ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ ሁኔታውን እንዲህ ይገልጹታል፦ "......ኣጤ ምኒልክ የትግራይን ሕዝብ እንደ ሕዝባቸው ኣልተመለከቱትም፤ ኣካባቢውም በሽፍቶች ዘረፋና በድርቅ ምክንያት ተራቁቶ ባድማ ሆኗል፤......"

የባሰው ግን በኋላ የሚመጣው ነገር ነበር፤ ይኸውም ሕዝቡና የኣካባቢው ተፈጥሮ ትንሽ ያገገመ መስሎ ሲታያቸው፣ 'ይኼ ኣካባቢ ከተጠናከረ የመንግሥትነት ጥያቄ ሊያነሳ ይችላል' በሚል ስሌት ይመስላል፣ ያለ ምንም መነሻና ማስጠንቀቂያ በብዙ ኣስር ሺዎች የሚቆጠር ወታደር (ነፍጠኛ) ሕዝቡ ላይ ኣፈሰሱበት፤ ውስጣዊ ምክንያቱ ግን ሕዝቡን በኢኮኖሚና በስነ-ልቦና ለመምታት ነበር፤

እያንዳንዱ ወታደር ወደ ኣንድ ገበሬ ቤት በምደባ ዓይነት ይገባል፤ ኣባወራው ገበሬ የሚያንገራግር ከሆነ ይገደላል፤ ከዚያ ወታደሩ የዚያ ገበሬ ቤት ቀለብተኛ ይሆንና የመረጠውን በግ እና ፍየል እያሳረደ ይቀለባል፤ የሕዝቡን የገንዘብ ኣቅም ለማዳከምና ለማራቆት ደግሞ ነፍጠኞቹ የሚጠቀሙባቸው ሁለት መንገዶች ነበሩ፤

የመጀመሪያው፣ ቀለብተኛው ነፍጠኛ ሊመገብ ማእድ ሲቀርብለት ገበሬው ወይም ሚስትየው እጁን ማስታጠብ ይኖርባቸዋል፤ እጅ ሲያስታጥቡ ታድያ እንዲሁ በነጻ ኣይደለም የሚያስታጥቡት። እጅ በሚያስታጥቡበት ጊዜ *'የእጅ ማስታጠቢያ'* ተብሎ 1 ብር (በዚያን ጊዜው) ለነፍጠኛው መክፈል ኣለባቸው፤ ከዚያ በኋላ የቀረበለትን ምግብ ተመግቦ ካበቃ በኋላ ኣረፍ ለማለት በገበሬው መደብ ላይ ይጋደማል፤ በኣንድ ጎኑ ተጋድሞ ከነበረ ወደ ሌላኛው ጎኑ ለመገልበጥ ሲፈልግ ራሱ ኣይደለም የሚገለበጠው፤ ገበሬው ወይም ሚስትየው ናቸው የሚገለብጡት፤ ታድያ ኣሁንም በብላሽ ኣይደለም የሚገለብጡት፤ *'የጎን መገልበጫ'* ተብሎ ኣሁንም ለነፍጠኛው 1 ብር ቁጭ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፤ በዚህ መንገድ የሕዝቡን ጥሪቱንና ገንዘቡን ሙልጭ ኣድርገው ካራገፉ በኋላ ወደ ምድብ ቦታቸው ሰሜን ሸዋ ተመልሰዋል፤ (ሕዝቡ ይኼን ወቅት "ዘመነ ሸ (ሸዋ ለማለት)" እያለ እንደሚጠራው ከተለያዩ ጽሑፎችና በኣፍ የሚነገሩ ታሪኮች ላይ ለመገንዘብ ተችሏል፤)

በዚህ ሂደት ትግራይ ወደ ኣስከፊ ድህነት ስትገባ በኣንፃሩ ሰሜን ሸዋ ግን ሃብታም እየሆነች ልትሄድ ችላለች። ነፍጠኞቹ ወደ ምድብ ቦታቸው ሲገቡ ብዙ ገንዘብ ይዘው ስለነበረ፣ ቤተሰባቸውን በጥሩ መንገድ ለማኖርና ልጆቻቸውንም በስነስርዓት ለማስተማር እንዳስቻላቸው ይታመናል። ስለዚህ፣ በኣሁኑ ወቅት የሰሜን ሸዋ ተወላጆች

ሆነው በትምህርትም ሆነ በሃብት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች፣ ለዚህ ደረጃ መድረሳቸው የትግራይ ሕዝብ ኣስተዋጽኦ እንዳለበት መዘንጋት የለባቸውም ።

### *ኣፄ ኃይለሥላሴ*

ኣፄ ኃይለሥላሴ ዳግማዊ ምኒልክ በኤርትራ የፈፀሙትን ስሕተት ለማረም ሲሉ ብዙ የደከሙ ቢሆንም፣ በትግራይ ላይ የሚከተሉት ፖሊሲ ግን ከኣፄ ምኒልክ ጋር ያመሳስላቸዋል፤ ሕዝቡን በከፍተኛ ግብርና ጨቋኝ ኣስተዳደር ኣማካኝነት ኣመፅን እንዲያስብ ከገፋፉት በኋላ የ *‘ቀዳማይ ወያነ’* ኣመፅ ሊቀጣጠል ችሏል፤ እንደ ወቅቱ ማዕከላዊ መንግሥት፣ ኣመፀኞቹን መውጋት ቅቡል ሆኖ ሳለ፣ ነገር ግን የኣፄ ኃይለሥላሴ መንግሥትም በጦርነት ሕግ የተወገዘውን ሲቪልና ያልታጠቀ ሰላማዊ ሕዝብን በገበያ ቀን በመቀለ ከተማ በኣውሮፕላን ቦምብ ደብድበዋል፤ ለዚህ ማስታወሻ እንዲሆን የገበያ ቦታ በነበረውና ድብደባ በተፈጸመበት ቦታ ዙሪያውን ያሉ ሱቆች ዲዛይን የመቃብር ቅርጽ የያዙ ናቸው ።

### *ደርግ*

ደርግ፣ ወታደራዊ መንግስት እንደመሆኑ ሁሉም ችግር በጠመንጃ የሚፈታ ነው ብሎ የሚያምን ይመስላል፤ *‘እምቢ ላለ ሰው ጥይት ኣጉርሰው’* የሚለው የደርጉ ኣባባልም ለዚህ እምነቱ ማሳያ ሊሆን የሚችል ይመስላል፤

የኤርትራን ችግር ከመሠረቱ የሚያውቁት ጀኔራል ኣማን ኣንዶም ሁኔታውን በጥንቃቄና በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥሩ መንገድ ከጀመሩ በኋላ ችግሩን በእብሪትና በጦረኝነት ለመፍታት ጀኔራሉን ካስወገደ በኋላ እንደሚታወቀው ኣገሪቱን ማለቂያ ወደሌለው ጦርነት እንዳስገባት ይታወቃል፤

ደርግ፣ ያልታጠቀ ሲቪል ሰላማዊ ማሕበረሰብን በጦር መሣሪያ ያጠቃበት ብዙ ኣብነቶችን ማቅረብ የሚቻል ሲሆን፣ የኣብነቶቹ ሁሉ ቁንጮ ግን የሐውዜን የገበያ ቀን ድብደባ ነው፤ በሐውዜን የተደበደበው የታጠቀ ተዋጊ ኃይል ሳይሆን፣ ለገበያ የወጣ ሲቪል፣ ያልታጠቀ፣ ሰላማዊ ሰው፣ ሴት፣ ወጣት፣ ህፃን፣ ሽማግሌ ሁሉንም ዓይነት የማሕበረሰብ ኣባል ያካተተ ሕዝብ ነበር ።

## እንደ ማጠቃለያ፣

ከላይ የተጠቀሰውን ታሪክ ለማንሳት የተፈለገው፣ ትክክለኛውን ታሪክ በማወቅ ኣስፈላጊውን እርምት ለመውሰድ እንዲቻል ለማገዝ ነው። ታሪካዊ ስሕተት በጫጫታ፣ ኣፍ በመካፈትና ኣቧራ በማስነሳት ኣይፈታም፤ ከስሜታዊነት በነፃ፣ በጽሞና በትኩረትና በእውነተኝነት በመነጋገር እንጂ።

እንደ ኣጋጣሚ ይሁን ወይም በሆነ ታሪካዊ መገጣጠም፣ ከላይ የተጠቀሱት ሦስቱ መሪዎች ራሳቸውን የሰሜን ሸዋ ተወካዮች ኣድርገው የሚመለከቱ ናቸው፤ በዚህ ረገድ ሲታይ፣ ሰሜን ሸዋ የሥልጣን ተቀናቃኞቿን ብቻ መውጋትና ማሸነፍ ሲገባት፣ "የነገሠ ንጉሴ ነው" ብሎ የሚኖረውን ሰላማዊ ህዝብ ጭምር በመቅጣቷና በመጉዳቷ ታሪካዊ ስሕተት ፈፅማለች። ለዚህም ካሣ ልትከፍል ይገባል ባይ ነኝ ።

ካሣ ሲባል ለያንዳንዱ ሰው የገንዘብ ካሣ ይሰጥ ማለት ሳይሆን ለማሕበረሰቡ የሚጠቅም፣ በጎ ፈቃድን የሚያሳይ፣ ተምሳሌታዊ የሆነ ካሣ ይሰጥ ለማለት ነው፤ ለዚህም በአሁኑ ወቅት በጥሩ ደረጃ ላይ የሚገኙ የሰሜን ሸዋ ተወላጆች ታሪካዊ ኃላፊነት ያለባቸው ይመስለኛል ።